# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 222 ነሐሴ 10 2004 ገጽ 1


**ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ የኢትዮጵያ ሠራዊት መኮንኖች፣ ነፃ የኢትዮጵያ ሠራዊት ንቅናቄ (ነኢሠን)በህቡዕ በመመሥረታቸው የተሰማውን ደስታ ይገልፃል። በሠራዊቱ ውስጥ ያላችሁ ሌሎች መኮንኖች እና ወታደሮች የነኢሠን አርዓያነት እንዲከተሉ ያበረታታል። የሠራዊቱ አባላት "የመሣርያችሁ አፈሙዝ ወደ ወያኔ ይዞር!" ይላል።**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የአዋሳ ከተማ ነዋሪዎች የክልሉን ፕሬዝዳንት ሽፈራው ሽጉጤን ሲያወግዝ ዋለ። ኢሃደግ በቃንም ብሎአል

በትናትናው እለት በአዋሳ ከተማ በጉዱማሌ አደባባይ በተከበረው የጫምባላ በዓል ላይ የተገኘው በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠር ህዝብ የክልሉን ፕሬዝዳንት ተፈራ ሽጉጤንና ወያኔ ኢሃደግን በጽኑ ሲያወግዝ እንደዋለ ለማወቅ ተችሎአል።

የሲዳማ ብሄረሰብ ባህላዊ የአዲስ አመት መግቢያ ቀን በሚከበርበት በዚህ የዘንድሮው የጫምባላ በዓል ላይ ከአዋሳና አካባቢው ቁጥሩ ወደ አምስት መቶ ሺህ የሚጠጋ ህዝብ እንደተሳተፈ የገለጹት ምንጮች ለበዓል ተብሎ የተሰባሰበው ህዝብ በበአሉ ላይ የተገኘውን የክልሉን ፕሬዝዳንት ተፈራ ሽጉጤንና ፓርቲውን ኢሃደግን በተለያዩ መፈክሮች ሲያወግዝ እንደዋለ ገልጸዋል።

ተፈራ ሽጉጤ አይወክለንም፤ ተፈራ ሽጉጤ አሁኑኑ ሥልጣንህን ልቀቅ ፤ ህዝብን ለማጋጨት የምታደርገው ሴራ በአስቸኳይ አቁም፤ ኢሃደግ ሰለቸን፤ ኢሃደግ በቃን፤ ወዘተ የሚሉ መፈክሮችን ሲያሰማ የዋለው የአዋሳና አካባቢው ህዝብ ተቃውሞ ሰልፍ ለማድረግ ከቤቱ የመጣ ሊመስል በሚችል ዲስፕሊንና ወኔ ድምጹን ከፍ አድርጎ መፈክሮቹን በሲዳማና በአማርኛ ቋንቋዎች ሲያስተጋባ ውሉ በሰላም ተበትኖአል ተብሎአል።

በተፈራ ሽጉጤ አስፈጻሚነት ወያኔ በህዝባችን ላይ እያደረሰ ያለውን ሰቆቃና አፈና በጽኑ ሲያወግዝ የዋለው የአዋሳና አካባቢው ነዋሪዎች ሲያሰሙት የነበረው የተቃውሞ መፈክሮች ህዝባችን በወያኔ አገዛዝ ላይ ያለውን ጥላቻና ተቃውሞ ለመግለጽ የሚችልበትን አጋጣሚ የሚጠባበቅ መሆኑን ያመለክታል ያሉ በርካቶች ናቸው። **(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)**

## አንጋፋው የህወሃት መስራች ስብሐት ነጋ መለስ ዜናዊ ያለበትን ሁኔታ እንደማያውቅ ለኢሳት ቴለቪዥን በሰጠው ቃለመጠይቅ ገለጸ

የመለስ ዜናዊ ከህዝብ እይታና ከሚዲያ መጥፋት በህይወት መኖሩን አጠራጣሪ አድርጎ ባለበት በአሁኑ ሰዓት በወያኔዎች ሰፈር እንደጠላት በሚቆጠረው የኢትዮጵያ ሳታላይት ቴለቪዥን ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ቃለመጠይቅ ለመስጠት የቻለው የመጀመሪያው ከፍተኛ የህወሃት ባለሥልጣን ስብሃት ነጋ ከአሁን ቀደም መለስ ዜናዊ በ10 ቀናት ውስጥ ወደ ስራ ገበታው ይመለሳል ብሎ ሰጥቶት የነበረው መግለጫ ስህተት እንደነበር ማመኑን ኢሳት ከትናትና በስቲያ ባስተላለፈው የዜና ዘገባው ይፋ አድርጎአል።

ኢሳት ከስብሃት ነጋ ጋር ባደረገው በዚህ የመጀመሪያ ቃለ መጠይቅ ደጋግሞ ያነሳው በረከት ስምኦን ባለፈው ሳምንት ለሚዲያ በሰጠው መግለጫ አለቃው መለስ ዜናዊ ከመጪው የኢትዮጵያ አዲስ አመት በፊት ወደ ስራ ገበታው ይመለሳል ማለቱን ተከትሎ የመረጃውን ትክክለኝነት እንዲያረጋግጥ ለማወቅ ነበር። ሆኖም ግን ከአሁን በፊት የሰጠውን አይነት የተሳሳተ መረጃ ለመድገም ምንም ፍንጭ ማሳየት ያልፈለገው ስብሃት ነጋ እኔ ሰለመለስ ዜናዊ የማውቀው ምንም መረጃ ስለሌለ በረከት ስሞን እንደገባበት ይወጣው በሚል አቋም መልሶ መላልሶ የማውቀው ነገር የለም ሲል ተደምጦአል። **(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)**

## "የወቅቱ የኢትዮጵያ አስተዳደር የፍትህ ጋዜጣን ማገዱ፤ በኢትዮጵያ ጭል ጭል ሲል የነበረው የፕሬስ ነፃነት ሙሉ ለሙሉ መዳፈኑን የሚያመለክት ነው" ሰል ኢነጋማ ገለጸ

በስደት የሚገኘው የኢትዮጵያ ነፃ ጋዜጠኞች ማህበር፡- "በፍትህ ጋዜጣና በአዘጋጁ ላይ እየተወሰደ ያለው እርምጃ፤ በኢትዮጵያ የፕሬስ ነፃነት መብት ጨርሶ መጥፋቱን የሚያረጋግጥ ክስተት ነው" በሚል ርዕስ ባወጣው መግለጫ፤ ፍትህ ጋዜጣ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ በኢትዮጵያ ብቸኛ የነፃ ፕሬስ አማራጭ በመሆን፤ የህዝብን የማወቅ መብት ተግባራዊ ለማድረግ የተጣለባትን ተጽ እኖና አፈና ተቋቁማ ስትንቀሳቀስ መቆየቷን አውስቷል።

ሃምሌ 12 ቀን 2004 ዓ.ም ከአንባብያን እጅ መድረስ የነበረባት የፍትህ ጋዜጣ እትም ግን፣ ለሕትመት ብዙ ሺህ ብሮች ከተከፈለ በኋላ፣ ከአቶ መለስ ጤና ጋር ተያይዞ ባጠናቀረችው ዘገባ ምክንያት መታገዷን አስታውሷል።

"ከዚህም በተጨማሪም፤ የዚህ መንግስት መቀለጃ **(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)**

## ባለ ሁለት አሃዝ የኢኮኖሚ ዕድገት ተደጋግሞ በሚነገርባት አገራችን ወደ አራት ሚሊዮን የሚጠጉ ዜጎች በምግብ እጦት እየተሰቃዩ መሆናቸውና አስቸኳይ ዕርዳታ ካላገኙ ህይወታቸው አደጋ ላይ ሊወድቅ እንደሚችል የወያኔ ግብርና ሚንስቴር ዴታ አስታወቀ

የግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትር ደኤታ ምትኩ ካሳ የረሃብ ችግሩን አስመልክቶ ነሃሴ 7/ 2004 ዓ.ም በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ እነዚህን በምግብ እጦት የሚሰቃዩ ወገኖች ለመታደግ በገንዘብ ሲተመን 190 ሚሊዮን ዶላር የሚፈጅ 314 ሺህ ሜትሪክ ቶን እህል እንደሚያስፈልግ በመጥቀስ ለጋሾች በአስቸኳይ እጃቸውን ይዘረጉ ዘንድ ልመናውን አቅርቧል።

ሚኒስትር ደኤታው በዚሁ ወቅት እንዳለው በምግብ እጦት የሚሰቃዩት ዜጎች ቁጥር ከአምናው ጋር ሲነጻጻር 16 በመቶ አሻቅቧል።

የተዛባ ዝናብ፣ የበልግ ምርት መቀነስ፣ ችግሩ በተከሰተባቸው አካባቢዎች የሚኖሩ ህዝቦች የመግዛት አቅም ማጣት በምትኩ በምክንያትነት ተጠቅሰዋል።ይሁንና ሌሎች የሚኒስቴሩ ባለሙያዎች ግን ምክንያቶቹ እነዚህ ብቻ አይደሉም፣ በተለይም በሱማሌ፣ በኦሮሚያና በደቡብ ክልሎች በየጊዜው የሚታዩ አለመረጋጋቶች በዋነኛ ምክንያትነት ሊጠቀሱ ይገባል ይላሉ።

እነዚህ በምግብ እጦት የሚሰቃዩ ወገኖች 41 ከመቶው በሱማሌ፣ 27 ከመቶ በኦሮሚያ፣ 10 ከመቶ በትግራይ፣ 8.1 ከመቶ በደቡብና 7.7 ከመቶው በአማራ ክልሎች የሚገኙ ናቸው።

የግብርና ሚኒስትሩ በቅርቡ በምግብ ሰብል እራሳችንን እንችላለን ሲል መግለጫ በሰጠ በአጭር ጊዜ በሚኒስትር ደኤታው እንዲህ ዓይነት ተቃራኒ መግለጫ መሰጠቱ የወያኔ ባለስልጣናት ሀገር ያወቀውን እውነት ለመሸፋፈን ምንያህል እንደሚዋሹና እርስ በእርሱ የሚጋጭ መግለጫ ያለ እፍረት እንደሚያወጡ አመላካች ነው።

## የኢትዮጵያ የመከላከያ ሰራዊት በሙሉ ዝግጅት በተጠንቅቅ እንዲቆም ትዕዛዝ ተላለፈ

የኢትዮጵያ ምድር ጦርና የአየር ኃይል ሠራዊት በሚገኝበት ቦታ ሁሉ በተለይ በአዲስ አበባና በአዲስ አበባ አካባቢዎች በተጠንቀቅ እንዲቆም ከመከላከያ ሚኒስቴር ጥብቅ ትዕዛዝ የተላለፈ መሆኑን አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኙ የመከላለከያና የደህንነት ምንጮቻችን በላኩልን ዜና ገለጹ። ይህ የታጠቁ የሰራዊቱን አባላት በየቦታዉ በቀጭን ትዕዛዝ ጥቃት ማድረስ በሚችሉበት ዝግጅት በተጠንቀቅ እንዲቆሙ ያደረገዉ ትዕዛዝ የተላለፈበት ትክክለኛ ምክንያት ምን አንደሆነ በዉል ተለይቶ ባይታወቅም የመከላከያ ሚኒስቴር ትዕዛዙን ሲያስተላልፍ ለሠራዊቱ የሰጠዉ ምክንያት የእስልምና እምነት ተከታዮች የሚያደርጓቸዉ እንቅስቃሴዎች የአገሪቱን ደህንነት ከፍተኛ አደጋ ላይ ጥሎታል የሚል ሰንካላ አሳማኝነት የሌላው ምክንያት እንደነበር ምንጮቻችን አክለዉ ገልጸዋል። አንድ አመት ሊሞላዉ ጥቂት ግዜ የቀረዉ የኢትዮጵያ እስልምና እምነት ተከታዮች የመብትና የነጻነት ንቅናቄ ህዝባዊ ተሳትፎ ከቀን ወደ ቀን በከፍተኛ ደረጃ እያደገ ቢመጣም ንቅናቄዉ ከቁጥጥር ዉጭ የሆነበትና የአካባቢዉን ሠላም ያደፈረሰበት አንድም ግዜ የለም። በሌላ በኩል ደግሞ በየሳምንቱ አርብ እለት በመስጊዶች ቅጥር ግቢ እና አካባቢ የሚደረገዉ ህዝባዊ የተቃዉሞ ሠልፍ ምንም አይነት መሳሪያ የታጠቀ ኃይል ያልተቀላቀለበት በመሆኑ ወያኔ ይህንን ፍጹም ሠላማዊ የሆነ ህዝባዊ የመብት ጥያቄ አንደ ብሔራዊ ደህንነት ጉዳይ መዉሰዱና ሠራዊቱን በከፍተኛ ጥንቃቄ ላይ እንዲቆም ማድረጉ ብዙ የፖሊቲካ ተንታኞችን ግራ ያጋባ ጉዳይ ሆኗል።

የመለስ ዜናዊ የጤንነት ጉዳይና አገሪቱን የሚመራዉ ማነዉ የሚሉት ሁለት ቁልፍ ጥያቄዎች ተገቢዉን ምላሽ ባላገኙበት ወቅት የተላለፈዉ ይህ ከፍተኛ ወታደራዊ የተጠንቀቅ ትዕዛዝ ያሳሰባቸዉ ብዙ ኢትዮጵያዉያንና አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኙ አያሌ ዲፕሎማቶች አገዛዙ የሰጠዉ ዉኃ የማይቋጥር ምክንያት ስላልተዋጠላቸዉ "**ምን ተፈጥሮ ይሆን**" የሚሉ የተለያዩ መላምቶችን መምታት ጀምረዋል። የምድር ጦርና የአየር ኃይል የመከላከያ ሰራዊት በተለይም አየር ኃይል የአገርን ድንበር ከደፈረ የዉጭ ጠላት ጋር እንጂ እጠብቀዋለሁ ብሎ ቃል ከገባዉ ህዝብ ጋር የሚፋጠጥ ኃይል ባለመሆኑ ብዙ ወታደራዊ ተንታኞች መከላከያ ሚኒስተር ለሠራዊቱ አባላት የሰጠዉን ምክንያት አልተቀበሉትም።

እንደ ብዙ የፖለቲካ ተንታኞች አባባልና ዉስጥ አዋቂ ምንጮች ከአዲስ አበባ በሚልኩልን መረጃዎች መሰረት የወያኔ አገዛዝ ይህንን ወታደራዊ የተጠንቀቅ ትዕዛዝ ያስተላለፈዉ እስከዛሬ ተድብቆ በሸፍንፍን የኖረዉ የመለስ ዜናዊ ጉዳይ በይፋ ለህዝብ ሲገለጽ አገሪቱ ዉስጥ ሊፈጠር **(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)**

# ወያኔ ለግድያ ቢዘጋጅም ሕዝብ ደግም ወያኔን ለማስወገድ ተነስቷል!!!

ግፈኛው እና ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ፣ ሠራዊቱ በከፍተኛ ተጠንቀቅ ላይ እንዲሆን ትዕዛዝ ሰጥቷል። በዚህ መሠረት የጦሩ የምድርና የአየር ኃይላት በአንደኛ ደረጃ ተጠንቀቅ ላይ ይገኛሉ። የመከላከያ ሚኒስቴር እና በተዋረድ ያሉ የሠራዊቱ መዋቅሮች፤ የዘመቻ እና የድርጅት መምሪያዎች እንዲሁም ከፍተኛና መስመራዊ መኮንኖች በተጠንቀቅ ትዕዛዝ በመጠባበቅ ላይ ናቸው። ለጦር መሣሪያ እና ለጥይት ማከማቻ ዲፖዎችም የሚደረገው ጥበቃ ተጠናክሯል። ወያኔ ለታላቅ ጦርነት እየተዘጋጀ ነው።

ይህ ሁሉ ለምን አሁን ሆነ? ምን አዲስ ነገር ተፈጠረ? ምክንያቶቹ ሁለት ናቸው።

1ኛ. በወያኔ አገዛዝ ላይ የሚቀርበው ሕዝባዊ ተቃውሞ እየበረከተ መምጣቱ፤ እና

2ኛ. መለስ ዜናዊን ለመተካት የሚደረገው ሽኩታ ወደ ጉልበት ያመራ ይሆናል የሚለው ስጋት ማየሉ ናቸው።

እንደሚታወቀው በወያኔ አገዛዝ ላይ የተነሳው ሕዝባዊ ተቃውሞ ከእለት እለት ሥር እየሰደደና እየዳበረ ዛሬ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሷል። በዚህ ረገድ የሙስሊሙ ማኅበረሰብ የሚያደረገው ተጋድሎ በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀስ ነው። የሙስሊሞች ጥያቄ አሁን የኢትዮጵያዊያን ሁሉ ጥያቄ ሆኗል። በየመስጊዶቹ እየጎመሩ ያሉት እቅስቃሴዎች ወደ አደባባይ መውጫቸው ተቃርቧል። ሚያዝያ 30 ቀን 1997ን የሚያስታውሱን ታላላቅ ሕዝባዊ ሰልፎች የምናይበት ጊዜ እየቀረበ ነው። መንገዶች ሁሉ ወደ መስቀል አደባባይ እያመሩ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ወያኔ እንደ ፈጣሪው የሚያመልከውን መለስ ዜናዊን አጥቶ ለሁኔታዎች ሁሉ ባይተዋር ሆኗል። መለስ በሃያ አንድ ዓመታት የሥልጣን ጊዜው ከሠራቸው ነገሮች አንዱ ራሱን አይነኬ እና አይተኬ ማድረግ ነበር። የመለስ ዜናዊ አይነኬነት ቀረ። አይተኬነቱ ግን አሁንም አለ።

የመለስ ዜናዊ አይተኬነት የወያኔ ሹማምንትን በሙሉ ዋጋ ቢስ አድርጎ ተተኪ አሳጥቶ ጭንቀት ውስጥ ጨምሯቸዋል። "እንኳንስ ዘንቦብሽ ድሮም ጤዛ ነሽ" እንዲሉ እንኳንስ በእንዲህ ዓይነት የውጥረት ወቅት ይቅርና ለትንሹም ኮሽታ የወያኔ ሹማምንት በጠመንጃ ጀርባ የመደበቅ ልማድ አላቸው። የአሁን ነጋሪ ጉሰማም የዚህ ጭንቀት ውጤት ነው።

ይሁን እንጂ ወያኔ በጠመንጃ የሚድንበት ወቅት አልፏል። ይህ ማለት ግን ለመግደል፣ ለማሰርና ለማንገላታት አይሞክርም ማለት አይደለም። የፈለገውን ቢያደርግ እንኳን ከእንግዲህ የኢትዮጵያ ሕዝብ በወያኔ የፈሪ ዱላ አይደነግጥም። እንዲያውም የወያኔ ዛቻ እና ማስፈራራት በቀጠለ መጠን ተጨማሪ ኢትዮጵያዊያን ትግሉን ይቀላቀላሉ።

ዛሬ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከጥቃት ለመከላከል የቆረጡ ኃይሎች አሉ። የእነዚህ ኃይሎች ጉልበት በየእለቱ እየተጠናከረ ነው። እነዚህን ኃይሎች የሚቀላቀል አዲስና ትኩስ ኃይል ቁጥር ከግዜ ወደ ግዜ እየጨመረ ነው።

ወያኔ ሠራዊቴ የሚለው አካልም ሙሉ በሙሉ በቁጥጥሩ ሥር ሊሆን አይችልም ። ለዚህም ምልክቶች እየታዩ ነው። የኢትዮጵያ የመከላከያ፣ የፖሊስና የደህንነት ኃይል አባላት ሠራዊቱ በጥቂት የወያኔ ከፍተኛ መኮንኖች አማካይነት የማፈኛና የመጨቆኛ መሳሪያ መሆን እንደሌለበት በማመን በቆራጥነት እና በኢትዮጵያዊነት ወኔ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን መሰለፋቸው በቅርቡ በህቡዕ የተቋቋመው ነፃ የኢትዮጵያ ሠራዊት ንቅናቄ (ነኢሠን) አብስሯል። ነኢሠን በመግለጫው እንደገለፀው ሁሉ የኢትዮጵያ መለዮ ለባሾች ለፍትህ፣ ለነፃነት፣ ለአንድነትና ለዲሞክራሲ የቆሙ ኃይሎችን አይወጉም። የኢትዮጵያ የጦር ኃይሎች አባላት የዚህ ዘረኛ አስከፊ ከፋፋይና በዝባዥ መንግስት መሳሪያ አይሆኑም።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ወቅታዊ የአገራችን ሁኔታዎች በመገምገም የሚከተሉትን ጥሪዎች ያደርጋል።

**ለኢትዮጵያ ሕዝብ**

የተጀመረው ትግል መፋፋም ይኖርበታል። የሙስሊሞች ጥያቄዎች የክርስቲያኖች፤ የክርስቲያኖችም የሙስሊሞች ነው። ስለዚህ በሃይማኖትም መከፋፈል ትተን ድምጾቻችንን በጋራ ማስማት መቀጠል ይኖርብናል። ወደ አደባባዮችና ስታዴሞች በብዛት መትመም ይኖርብናል። የትግላችን ዓላማም ወያኔን ማስወገድ መሆን ይኖርበታል።

**ለመከላከያ ሠራዊት**

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ የኢትዮጵያ ሠራዊት መኮንኖች፣ ነፃ የኢትዮጵያ ሠራዊት ንቅናቄ (ነኢሠን)በህቡዕ በመመሥረታቸው የተሰማውን ደስታ ይገልፃል። በሠራዊቱ ውስጥ ያላችሁ ሌሎች መኮንኖች እና ወታደሮች የነኢሠን አርዓያነት እንዲከተሉ ያበረታታል። የሠራዊቱ አባላት "የመሣርያችሁ አፈሙዝ ወደ ወያኔ ይዙር!" ይላል።

ከዚህ በፊትም በተደጋጋሚ እንዳነሳው ግንቦት 7 ዛሬም ትኩረታችን ያለው ወያኔን በማስገደድ ስልጣን እንዲለቅ ማድረግ፤ ያ ካልሆነ ደግሞ ማስወገድ ላይ መሆን ይኖርበታል ብሎ ከልብ ያምናል። ይህ ሲሆን ብቻ ነው ለሙብት ለነፃነትና ለእኩልነት የሚደረገው ትግል ግቡን የሚመታው።

ግንቦት 7 ለዚህ ዓላማ ቆርጦ ተነስቷል። በደል ግፍ የበዛበት፣ በእብሪተኛ ዘረኛ ሥርዓት ውስጥ መከራውን እንዲያ የተደረገው የአትዮጵያ ሕዝብም ለዚህ ዓላማ ቆርጦ እንዲነሳ ጥሪ ያደርጋል።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

---

## የአዋሳ ከተማ ነዋሪዎች የክልሉን ፕሬዝዳንት ሽፈራው ሽጉጤን . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

በትናትናው ዕልት የአዋሳ ህዝብ ባሰማው ተቃውሞ ምክንያት ወያኔ በክልሉ ያሰማራቸው ፖሊሶችም ሆኑ ሌሎች የጸጥታ ሰራተኞች ህብረተሰቡን ለመተናኮልም ሆነ ተቃውሞውን ለማስቆም ሲሉ ምንም አይነት እርምጃ ለመውሰድ አለመዘጋጀታቸው የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ በህዝባችንና በአገራችን ላይ እየፈጸማቸው ያሉት ወንጀሎች መለዮ ለባሹንም ክፍል እያስከፋ መምጣቱን አመልካች እንደሆነ ተገምቶአል። በአዋሳ ከተማ ውስጥ ከወራት በፊት ተነስቶ በነበረው ህዝባዊ አመጽ ምክንያት የተጀመረው ውጥረት አሁንም እንዳልበረደ ለማወቅ ተችሎአል።

## የኢትዮጵያ የመከላከያ ሰራዊት በሙሉ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

የሚችለዉን የፖለቲካ ቀዉስ ከወዲሁ ለመቆጣጠርና ህዝብን ለማስፈራራት መሆኑ ይገመታል። በተለይ መለስ ዜናዊን ማን ይተካዋል በሚለዉ ጥያቄ ዙሪያ የወያኔ አባላት ዉስጥና በሌሎቹ የኢህአዴግ ድርጅቶች ዙሪያ ከፍተኛ የስልጣን ሽሚያና ጭቅጭቅ ስለተፈጠረ ይህ የተጠንቀቅ ትዕዛዝ የአገሪቱን ጦርና የደህንነት ተቋሞች የሚቆጣጠሩ ኃይሎች የፖለቲካ ጡንቻቸዉን ለማሳየት የወሰዱት እርምጃ ነዉ የሚሉም አልታጡም። በሌላ በኩል ደግሞ የተጠንቀቅ ትዕዛዙ የተላለፈዉ አገር ዉስጥ ሊፈጠር የሚችለዉን የፖለቲካ ቀዉስ አስታክካ ኤርትራ በኢትዮጵያ ላይ ወረራ ትፍጽም ይሆናል ከሚል ፍራቻ በመነሳት ነዉ የሚሉ አንዳንድ ወታደራዊ ተንታኞች ቢኖሩም ይህም ምክንያት በጣም ልልና የማያሳምን ምክንያት መሆኑን ብዙዎች ይናገራሉ፡፡

---

## አንጋፋው የህወሃት መስራች ስብሐት ነጋ መለስ ዜናዊ ያለበትን ሁኔታ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

የአቦ ስብሃትን የኢሳት ቃለ መጠይቅ የተከታተሉ በርካታ ሰዎች ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት አስተያየት የመለስ ዜናዊ በህይወት መኖርም ሆነ አለመኖርን በ እርግጠኝነት መግለጽ የተሳናቸው አቦ ስብሃት መደበቅ የፈለጉት ነገር እንዳለ ከንግግራቸው መረዳት ይቻላል ብለዋል።

ጠቅላይ ሚንስትሩ ባይኖርም ምክትል ጠቅላይ ምንስትሩ ተክቶ በመስራት ላይ ነው ያለው አቦስብሃት ከጀርመን ድምጽ ሬዲዮ ጋር በቅርቡ አድርጎት በነበረው ቃለመጠየቅ የሥልጣን ዝ ው ውር ላይ ነን ማለቱን ክዶአል።

ቱባ ቱባ የወያኔ ባለሥልጣናት ስለ አለቃቸው መለስ ዜናዊ የተምታታና እርስ በርሱ የሚጣረዝ መግለጫ መስጠታቸው በመግፋት ላይ ባሉበት በአሁኑ ሰአት ሲ ኤን ኤን ዬመለስ ዜናዊ ዱካ ካለፈው ሰኔ ወር ጀምሮ እንደጠፋ ሰፊ የአየር ሰዓት ሰጥቶ መዘገቡ ታውቆአል።

ሲ ኤን ኤን በርካታ የህዝብ አስተያየቶችን አሰባስቤያለሁ በማለት ባሰራጨው ዘገባ በርካታ ሰዎች በመለስ ዜናዊ መጥፋት ግራ እንደተጋቡ የገለጸ ቢሆንም ብዙዎች የርሱን መጥፋት ለአገራቸው መልካም እድል ይዞ ይመጣል ብለው እንደሚያስቡ አልሸሸገም።

ይህ በዚህ እንዳለ በርካታ የወያኔ ባለሥልጣኖች ከህዝብ የዘረፉትን ገንዘብ ይዘው ለመሸሽ ሲሉ በ እጃቸው ያስገቡትን ገንዘብ በውጪ ምንዛሪ የመቀየር የተጠናከረ ዘምቻ ላይ እንዳሉ ለማወቅ ተችሎአል:: በዚህም ምክንያት በአገሪቱ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የውጪ ምንዛሪ እጥረት መከሰቱን የወያኔ ሚዲያዎች ሳይቀሩ ዜናውን እያናፈሱ ነው።

መለስ ዜናዊ ከህዝብና ከሚዲያ ከጠፋ ወዲህ በመላው አገሪቱ ውስጥ በስፋት በሚነዛው የመሞቱ ዜና ምክንያት ልጆቻቸውንና ሚስቶቻቸውን ከአገር ማስወጣት የጀመሩ ባለስልጣናት ቁጥርም ቀላል እንዳልሆነ ይነገራል።

የጎንደር ከተማ ከንቲባ ሆኖ ሲያገለግል የነበረው ሃብታሙ ገነቱ ተዲላ የተባል ግለሰብም በ እጁ የሚገኘውን በርካታ ገንዘብ ይዞ ወደ አሜሪካ አገር እንደገባ ቅርበት ያላቸው ምንጮች ገልጸዋል።

# ከጥሩ ወደ ታላቅ

## አንዳንድ ድርጅቶች ታላቅ ለውጥ ማምጣት ሲችሉ ሌሎቹ የሚያቅታቸው ለምንድነው?

**በንቅናቄዓችን ትምህርትና ሥልጠና የተዘጋጀ ( ክፍል 2)**

**እርከን አምስት: *ሥራ አስፈፃሚ* (Executive )**

- ትህትናንና ሙያዊ ብቃትን በማዳቀል ድርጅቱን ለዘላቂ ታላቅነት መምራት የሚችል

**እርከን አራት: *ውጤታማ መሪ* (Effective Leader)**

- የድርጅቱን ራዕይ በትጋት የሚከተል፤ ለከፍተኛ ጥራት የሚተጋ መሪ

**እርከን ሶስት: ብቁ *ሥራ* አስኪያጅ (Competent Manager)**

- ሰዎችንና ሌሎች ግብዓቶችን አስቀድሞ ለታሰበባቸው ግቦች ስሉጥ እና ፍሬዓማ በሆነ መንገድ ማደላደል የሚችል መሪ

**እርከን ሁለት: አስተዋፅዖው የጎላ የቡድን አባል (Contributing Team Member)**

- የግል ችሎታዎቹን ለቡድን የሚያውልና ከሌሎች የቡድኑ አባላት ጋር ተግባብቶ መሥራት የሚችል

**እርከን አንድ: ከፍተኛ ችሎታ ያለው ግለሰብ (Highly Capable Individual)**

- ችሎታዎቹን፣ እውቀቱንና ተሰጥዖዎቹን ተጠቅሞ ለመልካም ሥራ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ማበርከት የሚችል ግለሰብ

ከጥሩ ወደ ታላቅነት የተሸጋገሩ ድርጅቶች በሙሉ አምስተኛ እርከን ላይ የደረሱ የበሰሉ፣ የታመኑ፣ ትሁት አመራሮች አሏቸው። በተለይም በሽግግር ወቅት አምስተኛ እርከን ላይ የደረሰ አመራር መኖር ወሳኝ ነው። ድርጅቱ በንግድም ይሁን በማኅበራዊ አገልግሎት ወይም በሌላ ማናቸውም ዓይነት የሥራ መስክ ቢሰማራ ታላቅ ድርጅት እንዲሆን ታላላቅ መሪዎች ሊኖሩት ይገባል። የታላላቅ ድርጅት መሪዎች ራሳቸው ታላላቆች መሆን ይኖርባቸዋል።

"እርከን አምስት" ከፍተኛው የአመራር ደረጃ ይመለከታል። በዚህ ደረጃ ላይ ያለ ሰው ብቁ የሥራ አስፈፃሚ ነው። እዚህ ደረጃ ላይ የደረሰ ሰው ሙያዊ ብቃትን ከሥነምግባራዊ ትህትና ጋር አዳምሮ የያዘ ነው። እዚህ ደረጃ ላይ የደረሰ ሰው ህልሙ፣ ፍላጎቱ፣ ጥረቱ የድርጅቱ እድገት ነው። የዚህ ዓይነቱ ሰው ጥም የሚረካው በድርጅቱ እድገት ነው። እርከን አምስት መሪ የሥራ እንጂ "የጌጥ ፈረስ" አይደለም

**የእርከን አምስት አመራር ሁለት ዋና ዋና ባህሪያት**

**ባህሪ አንድ: *ሙያዊ ፍላጎት* / Professional Will/**

አምስተኛ እርከን ላይ ያለ መሪ

- ከጥሩ ወደ ታላቅነት የሚያሸጋግር ውጤት ማስገኘት ይችላል።
- የቱን ያህል አስቸጋሪ ቢሆንም እንኳን ለረዥም ጊዜ የሚቆይ የላቀ ውጤት የማስመዝገብ ቁርጠኝነት አለው።
- ለድርጅቱ ከፍተኛ የብቃት ደረጃ ያወጣና ከዚያ ደረጃ ላለመውረድ ይተጋል።
- ነገሮች ወደ መጥፎ አቅጣጫ ቢያመሩ፤ እቅዶች ሳይሳኩ ሲቀሩ ሰበብ ፍለጋ ወደ ሌሎች ሰዎች ሳይሆን ወደ ራሱ ይመለከታል። ለደረሱ ጥፋቶች ራሱ ኃላፊነት ይወስዳል።

**ባህሪ ሁለት: ትህትና/Personal Humility/**

አምስተኛ እርከን ላይ ያለ መሪ

- ትሁት ነው። ፈጽሞ አይታበይም።
- የቱን ያህል አስቸጋሪ ቢሆንም እንኳን ለረዥም ጊዜ የሚቆይ የላቀ ጽናትና ትዕግሥት አለው።
- ለታይታና ለዝና ሳይጨነቅ ሥራዉን በዝግታና በጥሞና ይከውናል።
- የግል ፍላጎቶቹን ከድርጅቱ ፍላጎቶች ጋር ያቀናጃል።
- ከራሱ በላይ ውጤታማ የሆነ ተተኪ መሪ ለመፍጠር ይጥራል
- ውጤት ሲያምር፤ ከታቀደው በላይ ሲሳካ ለስኬት ምክንያት የሆኑትን ለማመስገን ወደሌሎች ይመለከታል። ለተገኘው መልካም የሥራ ውጤት ሌሎችን ያመሰግናል፤ ይሸልማል።

**ምዕራፍ III: በመጀመሪያ "ማን" ... ከዚያ "ምን" /First Who . . . Then What/**

ከጥሩ ወደ ታላቅነት መጓዝ የሚፈልጉ ድርጅቶች በቅድሚያ "ማን አውቶቡሱ ውስጥ አለ?" ብለው ይጠይቁ። በቅድሚያ ተገቢ ሰዎች አውቶቡሱ ውስጥ ይገቡ፤ ተገቢ ያልሆኑት ይዉጡ ። ከዚያ በኋላ ስለጉዞዓቸው ይነጋገሩ።

ታላላቅ ውጤትን ያስመዘገቡ ድርጅቶች በሁሉ አስቀድሞ መድረሻቸውን ያወቁ፣ ራዕያቸው ያዩ፤ ተልዕኮዎቻቸውን በሚገባ የተረዱና ግቦቻቸውን በሚገባ የተረዱ ይሆናሉ የሚል ግምት ነበረን። በዚህ ጥናት የተገኘው ውጤት ግን ከዚህ የተለየ ነው። ድርጅቶቻቸውን ወደ ታላቅ ግብ ያደረሱ መሪዎች በመጀመሪያ የሚያነሱ ጥያቄ "የት መድረስ እንፈልጋለን?" ሳይሆን "ከማን ጋር እንጓዛለን?" ነው።

ድርጅት በአውቶቡስ ቢመሰል የመሪዎች የመጀመሪያ ሥራ መሆን ያለበት ትክክለኛ ሰዎች አውቶቡሱ ውስጥ መግባታቸውና በየተገቢው ቦታ መቀመጣቸውን፤ በአውቶቡሱ ውስጥ መገኘት የሌለባቸው ሰዎች ደግሞ ከአውቶቡሱ መውጣቸውን ማረጋገጥ ነው። ተገቢ ሰዎቻቸውን መያዛቸውን ካረጋገጡ በኋላ ነው "የት እንሂድ?" "እንዴት እንሂድ" .. እና የመሳሰሉ ጥያቄዎችን የሚመልሱት።

የላቀ ውጤት አስመዝጋቢ መሪዎች "ከምን" በፊት "ማን" ያስቀድማሉ። በተገቢ ሰዎች የተሞላ ድርጅት አስቸጋሪ የሆኑ ችግሮችን በጣጥሰው ማለፍ ይችላሉ። ተገቢ ባልሆኑ ሰዎች የተሞላ ድርጅት ግን የተፈጠሩለትንም እድሎች መጠቀም አይችልም። በተገቢ ሰዎች የተሞላ ድርጅት በጠመዝማዛ መንገድ መጓዝ፤ የስትራቴጂ ማሻሻያ ማድረግ አያቅተውም። ሁኔታዎች ተቀይረው መንገድ መቀየር ካስፈለገ ያለብዙ ችግር እስምምነት ላይ መድረስ ይቻላል። በተገቢ ሰዎች የተሞላ ድርጅት አባላቴን ወይም ሠራተኞቼን በምን ላነቃቃ የሚለው ችግር በአብዛኛው ከመነሻው ተቃልሎለታል። ሠራተኞቹ ወይም አባላት ውጫዊ ማነቃቂቃ ወይም ማበረታቻ እምብዛም የማይፈልጉ በራስ ተነሳሽነት መሥራት የሚችሉ ይሆናሉ።

በአንፃሩ ድርጅቱ የተሞላው ተገቢ ባልሆነ ሰዎች ከሆነ ድርጅቱ ትክክለኛ መንገድ ያዘ አልያዘ የትም ሊደርስ አይችልም። ብሩህ የሆነ ዓላማ ብሩህ ባልሆኑ ሰዎች፤ ትልቅ ዓላማ ትላልቅ ባልሆነ ሰዎች ከተያዘ ዋጋ የለውም።

ትልቁ የመሪዎች ችሎታ ብቁ አባላትን (ሠራተኞችን) እንዴት ማፍራትና ማበልጸግ እንደሚቻል ማወቅ ነው። የታላላቅ ድርጅቶች ዋነኛ ሃብት በሥነምግባር የታነጹቱ አባላቱ (ሠራተኞቹ) ናቸው። ትልቁ ኪሳራው ደግሞ ይህ የጎደላቸው አባላትን (ሠራተኞችን) ይዞ እየሄደ ከሆነ ነው።

ከጥሩ ወደ ታላቅነት የሚሸጋገሩ ድርጅቶች አባሎቻቸውን በማሳደግ ያምናሉ። በአባላት (በሠራተኛ) አስተዳደር ላይ ጥብቅ ናቸው፤ ጨካኞች ግን አይደሉም።

**ምዕራፍ IV: *መራሩን ሃቅ ይጋፈጡ* /Confront the Brutal Facts/**

ትላልቅ ህልሞችን ማለም ጥሩ ነው። ነገር ግን ሁሌም ህልሞች ከሃቅ ጋር መነፃፀር አለባቸው። ከመሪዎቹ ህልሞች ይልቅ ራሳቸው መሪዎች ሲታመኑ ተከታዮች ውጤትን ከመሪዎቹ መጠበቅ ይጀምራሉ። ከመሪዎቻቸው የሚጋሩት ህልም መሆኑ ይቀርና ውጤት ይሆናል። ከፋቱ ብዙ ነገር በመሪዎች ላይ በተጣለ መጠን ውጤት ማግኘት ይከብዳል።

ተጨባጩ ሃቁ መራር በሚሆንበት ወቅት ሰዎችን በብሩህ ራዕይ ማነቃቃት ይቻላልን? በዚህ ጥናት የተገኘው ውጤት "አይቻልም" የሚል ነው።

ከመጀመሪያው "ያሳፈሯቸው" ሰዎች ተገቢዎቹ ሰዎች ካልሆኑ ውብ ራዕይዎን በውብ ቃላት ቢናገሩም የሚሰማ ጆሮ አያገኙም። ከመጀመሪያው ሰዎችዎን በአግባቡ መርጠው ከሆነ ግን ይኸ ችግር አይገጥሞትም። ድርጅቱ አስቸጋሪ ፈተና በሚገጥመው ወቅት ሰዎችዎ የእርስዎን ማበረታቻ ሳይጠብቁ ራሳቸውን በራሳቸው ያነቃቃሉ።

እርግጥ ነው ብሩህ ራዕይ ለአመራር በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። መሪዎች የድርጅታቸውን ራዕይ በሚገባ መግለጽ መቻል አለባቸው። ችግርን መጋፈጥ መቻልም የዚያኑ ያህል አስፈላጊ ጉዳይ እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል። ችግር በገጠመ ጊዜ ሁሉ ማበረታቻና ማባበያ የሚፈልግ አባል (ሠራተኛ) የሞላበት ድርጅትን ታላቅ ማድረግ አይቻልም።

በታላላቅ ድርጅቶች ውስጥ ሃቅ የቱን ያህል መራር ብትሆን የመሰማት (የመደመጥ) እድል አላት። "ሃቅ አለኝ" የሚል ሁሉም መሰማት (መደመጥ) ይኖርበታል።

እንዴት ነው ሃቅ የሚሰማበት ሁኔታ መፍጠር የሚቻለው?

1. በጥያቄዎች እንጂ በመልሶች አይምሩ። የታላቅ ድርጅት መሪ መሆን ማለት ለችግሮች ሁሉ ምላሽ ያለው ሰው መሆን ማለት አይደለም። መልሶችን ሳይሆን ጥያቄዎችን ይዘው ወደ አባላት (ሠራተኞች) ይቅረቡ። መፍትሄዎችን ከእነሱ ጋር ይፈልጉ።
2. በማስገደድ (በመጫን) ሳይሆን በውይይትና በክርክር ይምሩ። ታላላቅ ድርጅቶች በውስጣቸው ከፍተኛ ውይይትና ክርክር የሚደረግባቸው ናቸው። ክርክሮቹም የይስሙላ ሳይሆኑ ሃሳብ "የሚሸጥባቸው" እና "የሚገዛባቸው" ገበያዎች ናቸው።
3. ውንጀላ የሌለበት ምርመራ ማካሄድ። ስህተቶች ከተፈፀመው የስህተቶችን ምንጭ መርምሮ ማግኘትና የእርምት እርምጃ መውሰድ ይገባል። የምርመራዎች/የግምገማዎች/ ግብ መወነጃጀል ሳይሆን መማማር መሆን ይኖርበታል። ስለሆነም ምርመራዎችዎ አበረታች መሆን ይገባቸዋል።

"ቀይ ባንዲራ" የማቆም ባህል መገንባት። ታላላቅ ድርጅቶች ከሌሎች የተሻለ የመረጃ ምንጭ የላቸውም። የሚለዩት ለመረጃ ባላቸው ክብር ነው። የማይናቁ መረጃዎች አሉ። በቂ መረጃ በተገኙ ጊዜ ደግሞ ወዲያዉኑ ተገቢው እርምጃ የመውሰድ ባህል መገንባት ይገባል።

**ምዕራፍ V: የጃርቷ ነገረ-ሃሳብ /The Hedgehog Concept/**

ስለጃርት እና ቀበሮ የተነገረውን ጥንታዊውን የግሪክን ተረትን ያስታውሳሉ?

( ክፍል 3 ሳምንት ይቀጥላል)

## በወያኔ አባላት መካከል በሚደረገዉ የስልጣን ሽሚያ ዉስጥ በቀጥታ ተሳታፊ ለመሆን ስዩም መስፍን ቻይናን ለቅቆ አዲስ አበባ መግባቱ ተነገረ

በወያኔ የስልጣን ተዋረድ ዉስጥ ከፍተኛ ቦታ እንዳለዉ የሚነገርለት ስዩም መስፍን መለስ ዜናዊን ለመተካት በወያኔ ዉስጥ በሚደረገዉ የርስ በርስ የስልጣን ሽኩቻ የቅርብ ተሳታፊ ለመሆን የቻይና አምባሳደርነቱን ቦታ ለግዜዉ ትቶት አዲስ አበባ መግባቱን አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኙ ለወያኔ ቅርበት ያላቸዉ ምንጮቻችን ገለጹ። ለመለስ ዜናዊ ቅርበት ያለዉና የረጂም ግዜ ታማኝ አገልጋዩ የሆነዉ ስዩም መስፍን መለስ ዜናዊን ይተካሉ ከሚባሉት የወያኔ ሹሞች አንዱ ሲሆን ቻይና መዲና ዉስጥ ተቀምጦ አዲስ አበባ ዉስጥ በቀድሞ የበረሐ ጓደኞቹ መካከል የሚደረገዉን የስልጣን ፉክክር በርቀት መከታተል ሆዱ አላስችል ብሎት ቻይና ዉስጥ ያለዉን የኢትዮጵያ ኤምባሲ በር ቆልፎ አዲስ አበባ የገባዉ ባለፈዉ ሳምንት መገባደጃ ላይ አንደነበር ዉስጥ አዋቂ ምንጮቻችን አክለዉ ገልጸዋል። በአሁኑ ወቅት በስዩም መስፍን፤ በአባይ ወልዱ፤ በብርሐነ ገ/ክርስቶስ፤ በአርከበ እቁባይና በአዜብ መስፍን መካከል ከፍተኛ የስልጣን ይገባኛል ትግል እየተካሄደ መሆኑን ከአዲስ አበባ የሚደርሱን ዘገባዎች ያስረዳሉ።

አዜብ መስፍን ኤፈርት በሚባል ምህጻረ ቃል የሚታወቀዉ የወየኔ የኤኮኖሚ ተቋም ፕሬዚዳንትና የህወሀት ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ብትሆንም የጎንደር ልጅ በመሆኗና ቀድሞዉንም ቢሆን የሷ የፖለቲካ ጡንቻ ከባሏ ከመለስ ዜናዊ በብድር የተገኘ በመሆኑ እሱ በሌለበት ቦታ እሷን ከቁም ነገር የሚቆጥሩ የወያኔ መሪዎች እጅግ በጣም ትቂት በመሆናቸዉ እንኳን መሪ ልትሆን ቀርቶ የዘረፈችዉን የህዝብ ሀብት በቅጡ ማስተዳደር አትችልም እያሉ ብዙ በቅርብ የሚያዉቋት ሰዎች እየተናገሩ ነዉ።

ለወያኔ ቅርበት ያላቸዉ ምንጮቻችን እንደሚናገሩት ከሆነ ወያኔዎች ኢትዮጵያን ረግጠን መግዛት አለብን በሚለዉ መሠረታዊ አላማቸዉ ብዙም የሚለያዩ አይመስልም፤ ደግሞም በኢህአዴግ ዉስጥ ያለዉ ዋናዉን የመሪነት ቦታ ከህወሀት ፓርቲ ዉጭ የመጣ ሌላ ሰዉ አንዲይዘዉ በፍጹም አይፈልጉም። ስለሆነም ዛሬ ስዩም መስፍንን ከቻይና ጎትቶ ያስመጣዉ ዋናዉ ጉዳይ የአገሪቱ መሪ እኔ መሆን አለብኝ የሚለዉ በእኔነት ላይ የተመሰረተዉ ስግብግበነት ነዉ አንጂ ኢትዮጵያ ካለመሪ መቆየት የለባትም የሚል አርቆ አስተዋይነት ወይም ለአገር አሳቢነት አይደለም። ዛሬ አገር ዉስጥም ሆነ ከአገር ዉጭ ያሉ የወያኔ አባላትና ደጋፊዎች ትልቁ ስጋት ስልጣን ከእጃችን ይወጣ ይሆን የሚል የፍራቻ ጥያቄ አንጂ አገሪቱ ለረጂም ግዜ ካለመሪ ስትቆይ ሊፈጠር የሚችለዉ የደህነንትና የአገር ፀጥታ ጉዳይ አለመሆኑ የወያኔዎች አላማ ዝርፍያና ሀብት ማካበት አንጂ አገርን ማዳን አለመሆኑን ብዙዎች ሙሉ በሙሉ የሚስማሙበት ጉዳይ ሆኗል።

በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ ህግ መንግስት ጠ/ሚኒስትሩ በሌለበት ምክትል ጠ/ሚኒስትሩ ተክቶ ይሰራል ቢልም ዛሬ አገሪቱን በኮሚቴ የሚመሩት ብርሀኔ ገ/ክርስቶስ፤ ሳሞራ የኑስ፤ ንዋይ ገብረአብና ስዩም መስፍን መሆናቸዉ ከደቡብ ህዝቦች ዲሞክራሲያዊ ግንባር የመጣዉ ኃ/ማሪያም ደሳለኝ ለይስሙላ ብቻ የተቀመጠ የመለስ ዜናዊ አሻንጉሊት መሆኑን ብዙዎች በግልጽ የሚናገሩት ግዳይ ሆኗል። መለስ ዜናዊ እንደዛሬዉ ከፖለቲካ አዳባባዮች ላይ ከመሰወሩ በፊት በተደጋጋሚ ስሙ ይጠቀስ የነበረዉ ኃ/ማሪያም ደሳለኝ ከቅርብ ግዜ ወዲህ ደብዛዉ መጥፋቱ ኃ/ማሪያም ደሳለኝ ብቻ ሳይሆን ብዙዎች የሱ አይነቶቹ ታማኝ ሎሌዎች ሲፈለጉ ተጎትተዉ የሚመጡ አለዚያም አንደ አሮጌ መኪና ተገፍተዉ የሚጣሉ ዕቃዎች ናቸዉ የሚለዉ አመለካከት የብዜ ኢትዮጵአዉያን እምነት ሆኗል።

## የመለስ ዜናዊን የወደፊት ዕጣ አስመልክቶ ሊፈጠር የሚችለዉን ቀዉስ በመፍራት የወያኔ ባለኀባቶችና የዉጭ አገር ሰዎች ገንዘባቸዉን በዶላር እየመነዘሩ ከአገር የማሸሽ ስራቸዉን አሁንም እንደቀጠሉ መሆኑ ተነገረ

ኢትዮጵጵያ ዉስጥ ጦሩን ጨምሮ በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች የሚታየዉን ህዝባዊ አለመረጋጋት በመፍራትና በተለይ የስርአቱ ቁንጮ የሆነዉ የመለስ ዜናዊ መሰወር ያሳሰባቸዉ የአገር ዉስጥና የዉጭ ባለኃብቶች ከዚህ ቀደም ታይቶ በማይታወቅ ፍጥነትና ብዛት ገንዘብ ከአገር ዉስጥ ማሸሽ መጀመራቸዉን አዲስ አበባ ዉስጥ በባንኮችና በሌሎች የገንዘብ ድርጅቶች ዉስጥ የሚሰሩ አገር ወዳድ ኢትዮጵያዉያን አጋለጡ፡፡ የወያኔ ስርአት ሹማምንትና ለስርአቱ ቅርበት ያለቸዉ ባለኃብቶች ያለቸዉን የፖለቲካ ስልጣን በመጠቀምና በባንኮች ላይ በተለይ በብሔራዊ ባንክ ላይ ተፅዕኖ በማሳደር ገንዘባቸዉን በዶላር እየመነዘሩ ከአገር ማሸሽ መጀመራቸዉ የአገሪቱን ኤኮኖሚ በከፍተኛ ደረጃ እየጎዳ መሆኑ እየተነገረ ነዉ። በተለይ ኢትዮጵጵያ ህዝብ የዋጋ ግሽበቱ በፈጠረዉ የኑሮ ዉድነት በሚሰቃይበት በአሁኑ ወቅት የተጀመረዉ የገንዘብ ማሸሽ ህደት አገሪቱን ታይቶ ወደማይታወቅ የምጣኔ ኃብት ቀዉስ ዉስጥ ሊከትታት አንደሚችል ብዙ የምጣኔ ኃብት ኤክስፐርቶች እያስጠነቀቁ ነዉ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የባለስልጣኖችን የገንዘብ ማሸሽ ዘመቻ በማስታከክ ጥቁር ገበያ ዉስጥ የወጭ ምንዛሪ በመቀበልና መለወጥ ስራ ላይ የተሰማሩ ነጋዴዎች በአጭር ግዜ ዉስጥ ወደ ቱጃርነት የተለወጡ መሆናቸዉን የግንቦት ሰባት ድምጽ ዘጋቢ ከአዲስ አበባ በላከልን ዜና ገለጸ። ጥቁር ገበያ ዉስጥ ለወትሮዉ በአስራ ሰባት ብር ይገዛ የነበረዉ አንድ የአሜሪካን ዶላር በአሁኑ ግዜ እስከ ሃያ አንድ ብር በመድረሱን ዘጋቢያችን አክሎ ገልጿል። በሌላ በኩል ደግሞ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቱ ስልክ ደዉለን ያናገርናቸዉ አንድ የኤኮኖሚክስ ምሁር የአገሪቱ የስልጣኝ ሽግግር ጉዳይ እልባት ካላገኘና የዶላር ማሸሹ ስራ በዚህ ፍጥነትና ብዛት ከቀጠለ አገሪቱ ለነዳጅ፤ ለህክምናና ለሌሎችም አስፈላጊ እቃዎች ማስመጫ የምትከፈለዉ የዉጭ ምንዛሪ ላይኖራት ይችላል የሚል ከፍተኛ ስጋት እንዳለባቸዉ ተናገረዋል። በስግብግቦችና በራስ ወዳዶች የግል ፍላጎት ላይ ተመስርቶ የተዋቀረዉ የኢትዮጵያ ኤኮኖሚ የመዉደቂያዉ የመጨረሻ ምዕራፍ ላይ መድረሱን የተናገሩት እኚህ ምሁር አገሪቷን ከዉድቀት ህዝቦቿን ደግሞ ከስደትና ከድህነት የማላቀቅ ግዜ አሁን መሆኑን በድፍረት ተናግረዋል። በኢትዮጵአ ኤኮኖሚ ላይ ሰፋ ያለ ጥናት ያደረጉት እኚህ የኤኮኖሚክስ ምሁር የወያኔ ባለስላጣኖች ብዛት ያለዉ ዶላር ከአገር ማሸሽ ከጀመሩ የሰነበቱ መሆኑን ተናግረዉ ይህ በቅርቡ የተጀመረዉ የገንዘብ ማሸሽ ዘመቻ ግን በፍጹም ታይቶ የማይታወቅ መሆኑን ተናግረዋል። ምሁሩ ይህ ችግር በአጭር ግዜ ዉስጥ መፍትሄ ሊያገኝ የሚችል ይመስልዎታል ወይ ተብለዉ ሲጠየቁ - ወንጀለኛዉ ወይም የችግሩ ባለቤትና መፍትሄ ፈላጊዉ አንድ ስለሆኑ መፍትሄ በቃላሉ የሚያገኝ ችግር አይመስለኝም ብላዋል።

## "የወቅቱ የኢትዮጵያ አስተዳደር የፍትህ ጋዜጣን ማገዱ፤ በኢትዮጵያ (ከገፅ 1 የዞረ)

በሆነው ፍርድ ቤት የታተመው 30 ሺህ ጋዜጣ እንዲቃጠል ተፈርዶበታል" ያለው ኢነጋማ፤ በዚህ በኩል ፍትህ ጋዜጣ፣ በአገራችን በፍርድ ቤት ትዕዛዝ እሳት እንድትለበለብ የተፈረደባት የመጀመሪያዋ ጋዜጣ ናት"ብሏል።

ይህ ሁሉ ሆኖ የፍትህ ሚኒስትር ባለስልጣናት ጋዜጣው በነፃነት ስራውን መቀጠል እንደሚችል በአንደበታቸው ቢገልጹም፣ አገዛዙ ግን በማተሚያ ቤቶች ላይ በፈጠረው ስውር ጫና ምክንያት ደፍሮ ጋዜጣዋን የሚያትም ድርጅት ባለመገኘቱ በተዘዋዋሪና በይፋ ፍትህ ጋዜጣ በመንግስት ታግዳለች-ብላል ኢነጋማ።
ገዥው ፓርቲ ድህረ ምርጫ 97ን ተከትሎ በምርጫው ለደረሰበት ሽንፈት በግልፅ ተጠያቂ ያደረገው የነፃ ፕሬስ ጋዜጦችን እና የሙያ ማህበራትን እንደነበር ያስታወሰው ኢነጋማ፤ እንደዛሬዋ ፍትህ ሁሉ በርካታ ጋዜጠኞች ታስረውና ጋዜጦችም እገዳ ተደርጎባቸው ከገበያ ውጪ መሆናቸውን ጠቅሷል።
ከነዚህ መካከል ነፃነት፣ ኢትኦጵ፣ አባይ፣ ሳተናው ምኒልክ፣ አስኳል፣ ጦማር፣ አዲስ ዜና፣ ጦቢያና ልሳነ -ሕዝብ በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱ መሆናቸውን ያወሳው ማህበሩ፤ በተለይ ኢትኦጵ ጋዜጣ የ130 ሺህ የህትመት ትዕዛዝ ሰጥቶ በመታተም ላይ እንዳለ በደህንነቶች ጣልቃ ገብነት በተሰጠ ትዕዛዝ ህትመቱ እንዲቋረጥና የታተሙትም ጋዜጦች እንዲወረሱ መደረጉን አትቷል።

የታሰሩት ጋዜጠኞች ከተለቀቁ በኋላ በሁለተኛው የነፃ ፕሬስ ምዕራፍ ብቅ ካሉት ጥቂት ጋዜጦች "ፍትሕ" በግንባር ቀደምትነት እንደሚጠቀስ ኢነጋማ ጠቁሟል።

የአዲስ ነገር እና የአውራምባ ታይምስ አዘጋጆችና ጋዜጠኞች በየጊዜው በደረሰባቸው ጫና አገር ጥለው በመሰደድ ጋዜጦቹ ሲዘጉ የስርዓቱ አራማጆች፡- "ውጭ ለመውጣት በመፈለጋቸው ነው" ማለታቸውን ያወሳው ኢነጋማ፤ ይሁንና እንዲያ ከተባሉት አንዳንዶቹ በተሰደዱበት ተጨማሪ ክስና የቅጣት ውሳኔ አልቀረላቸውም"ብሏል።

"ጋዜጠኛ ውብሸት ታዬን፣ ርዕዮት አለሙንና እስክንድር ነጋን "አሸባሪዎች" ብሎ ክስ የመሰረተው የወቅቱ አስተዳደር የፍትህ ጋዜጣን ማገዱ፤ በኢትዮጵያ ጭል ጭል ሲል የነበረው የፕሬስ ነፃነት ሙሉ ለሙሉ መዳፈኑን የሚያመለክት፤ ብሎም አምባገነኑ ስርዓት በግልፅ መንግስት ያልፈለገውን መፃፍና ማሳተም እንደማይቻል ያረጋገጠበትና የአፈናው ደረጃ እየጨመረ መሄዱን ያሳየበት ነው"ብሏል - በስደት ያለው ኢነጋማ።

"በአገራችን የፕሬስ ነፃነት እንዲረጋገጥ እና የዜጎች ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ ህጋዊ መብት እንዲከበር መታገል ፤የጋዜጠኞች ተልዕኮ ብቻ እንዳልሆነ ሁሉም ይገነዘበናል ብለን እናምናለን" ያለው ኢነጋማ፤ ስለዚህም ለእውነት ተቆርቋሪ የሆናችሁ ኢትዮጵያውያን በሙሉ፡- ፍትህ ጋዜጣን አግደው እና ዋና አዘጋጁ ተመስገን ደሳለኝ ባልቀረበበት ችሎት ተሰይመው- ክስ በመመስረት፣ በፍትህ ስም ፖለቲካዊ እርምጃ ለመውሰድ እየተሰናዱ ያሉትን ዳኞች በመቃወም እና ህዝባቸውን በቅንነት ስላገለገሉ በ"ሽብርተኛነት" ተወንጅለው መስዋዕትነት በመክፈል ላይ ከሚገኙት የነጻ ፕሬስ ጋዜጠኞች ጎን በመቆም፤ አጋርነታችሁን እንድታሳዩ እንጠይቃለን!" በማለት ህዛባዊ ጥሪ አቅርቧል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz
<u>አጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org